## ስለ አማኑኤል የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ቤ/ክ አጀማመር

የአማኑኤል የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ቤ/ክ በክርስቶስ የወንጌል መሰረት ላይ በዋሽንግተን ዲሲ ሜትሮ ኤርያ አካባቢ የተተከለችው፣ወንጌልን ላልደረሳቸው ለማድረስ እግዚአብሔር በጠራቸውና ራእዩን በሰጣቸው በወ/ም አበራ ተሰማና(በአሁኑ ጊዜ ፓስተር)በባለቤታቸው በእህት ሣራ ባህታ አገልግሎት ነው፡፡ወ/ም አበራና እህት ሣራ በDC ባለችው ባለችው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤ/ክ በአባልነትና በአገልግሎት ለአሥራሃንድ አመት ያህል ያገለገሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ወገኖች እግዚአብሔር በሰጣቸው የአገልግሎት ሸክም፣በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት በመቃተትና በመትጋት ቆይተው ራእያቸውን ለኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤ/ክ በዲሲ ለሚገኙ ፓስተሮችና ሽማግሌዎች አስታወቁ፡፡በቤ/ክርስቲያኒቱም አመራሮች ተቀባይነት በማግኘቱ በጠቅላላው ጉባኤ ፊት ጀነዋሪ 31/1993 ዓም ቤ/ክርስቲያን እንዲተክሉና አገልግሎታቸውን እንዲጀምሩ በጸሎት ተሸኝተዋል፡፡

ወ/ም አበራና እህት ሣራም በጸሎት ከሚያግዟቸው አያ ይርጋ ደስታና ጋሼ ማሞ ታደሰ ጋር ሲጸልዩ በመቆየት የአምልኮ ቦታ ሲያፈላልጉ ቆይተዋል፡፡በኋላም በ 310 TULIP AVE.TACOMA PARK,MARYLAND ቦታ በመገኘቱ የመጀመሪያው አጥቢያ በአፕሪል 4/1993 ዓም ወ/ም አበራ ተሰማና እህት ሣራ ባህታ አብረዋቸው በጸሎት ሲተጉ በነበሩት አያ ይርጋ ደስታና ጋሽ ማሞ ታደሰ ጋር ሆነው በእግዚአብሔር ፊት ተስማምተው በቦታዋ በጸሎት እየተጉ በዚያው ቤ/ክርስቲያኒቱ ተተከለች፡፡በዚህ ቀን በቃሉ ያገለገሉን ቄስ ዶ/ር ምትኩ ዘለቀ ሲሆኑ፣ፕሮግራሙን በመምራት ደግሞ ያገለገሉን ወንድም ተፈራ ወንድሙ ናቸው፡፡

በአሁኑ ሰዓት እህት ሣራ ሩጫቸውን ጨርሰው በ ኦገስት 2/ 1996 ዓም አንቀላፍተዋል፡፡ወንድማችን ጋሼ ማሞም በ 2001 ዓም፣ እንዲሁም ወንድማችን አያ ይርጋ ደስታ በ ኤፕሪል 2002ዓም ሩጫቸውን ጨርሰው አንቀላፍተዋል፡፡

ቤተክርስቲያኒቱ ዋና ትኩረትዋ ላለችበት አካባቢ ወንጌልን ማሰራጨትና በኢትዮጵያና በአካባቢው ባሉ ሀገሮችም ውስጥ ደግሞ የሚሽን ሥራ መሥራት ከጌታ የተቀበለችው አደራ ነው፡፡

የአማኑኤል የኢትዮጵያ ወንጌላዊት የአምልኮ አገልግሎት ለመስጠት በ 4/11/93 በተተከለችበት እለት በበራሪ ወረቀትና በጥሪ የተገኙ ሰዎች ወደ 70 ይሆናሉ፡፡በዚህ እለት ለቤተክርስቲያኒቱ አባባ አርቲኒ የመጽሐፍ ቅዱስ ስጦታን አበርክተዋል፡፡አባባ አርቲኒ ትልቅ የሚሽን ልብ ያላቸው ከቤ/ክርስቲያኒቱ ጋር የሚሳተፉ አባት ነበሩ፤ዛሬ አባባ አርቲኒ አገልግሎታቸውን ፈጽመው በፌብረዋሪ 2/2012 ዓም ወደ ጌታ ተሰብስበዋል፡፡በዚህ የሚሽን ሥራ ውስጥ አያ ይርጋና አባባ አርቲኒ በገንዘባቸው በጸሎት በማቴሪያል የሚሽንን ሥራ ለመሥራት ከቤተክርስቲያኗ ጋር አብረው የቆሙና የተሳተፉ አባቶች ነበሩ፡፡

ይሄ ሁሉ የሚያሳየው የቤ/ክርስቲያኒቱ ጥሪ አንዱ በሚሽን ሥራ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ታድርግ እንደነበረ ነው፤ዛሬም ቢሆን ቀጥላለች ወደፊትም ትቀጥላለች፡፡ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን፡፡

የአማኑኤል የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤ/ክ አገልግሎት በጀመረች በዓመቱ ለመጀመሪያ ጊዜ አሥራ ሦስት ሰዎችን አስተምራ ያጠመቀችበት ወቅት ነበር፤እነዚህ የቤ/ክርስቲያኒቱ የመጀመሪያ አዳዲስ አባሎች አሁንም በቤ/ክርስቲያኒቱ ውስጥ በተለያዩ አገልግሎት ዘርፎች በታማኝነት እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡በተለይ ደግሞ በዚህች ቤ/ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ቤታቸውን ጊዜያቸውን ያላቸውን ሁሉ ለሰጡት ወንድም ተፈሪ አበበና እህት ተናኜ ለብዙዎች እንደምሳሌና በረከት የሚታዩ ናቸው፡፡

የአማኑኤል የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤ/ክርስቲያን በታኮማ ፓርክ ሜሪላንድ ስድስት አመት አገልግሎት በመስጠት ከቆየች በኋላ በ ኤፕሪል 21/ 1999 ወደ 915 ኖርዝ አክላንድ ስትሪት አርሊንግተን ቨርጂኒያ መጣች፡፡ከአርሊንግተን ቨርጂኒያ የአምልኮ ቦታ በመግዛት በ ጁላይ 15/ 2015 ወደ 5411 ፍራንኮኒያ ሮድ አሌክሳንደሪያ ቨርጂኒያ የራሷን የአምልኮ ቦታ በመግዛት አድገቷንና የአገልግሎቷን ስፋት እያሳየች ትገኛለች፡፡

በአማኑኤል የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤ/ክርስቲያን በተለያዩ የአገልግሎት ክፍሎች ሁሉ በየቡድኑ ብዙ ወንድሞችና እህቶች በየጊዜው ለእግዚአብሔር ሥራና መንግሥት ዋጋ በመክፈልም ውጤት በማምጣት ከእነዚህ ወገኖች ጎን በመቆም ለእድገቷ አስተዋጽኦ ያደረጉ እንዳሉ አይዘነጋም፡፡የሁሉንም ሥም ዝርዝር መጻፍ ባይቻልም በቤ/ክርስቲያኒቱ መዝገብ ስለሚገኙ እግዚአብሔርን ስለእነርሱ እናከብራለን፡፡የዚህች ቤ/ክርስቲያን እዚህ መድረስ የአንድና የሁለት ወይም የሦስት ሰዎች ውጤት ብቻ ደግሞም እንዳልሆነ

ሁሉም ቅዱሳን በቅንነት የሚረዱትና የሚያውቁት እውነት ነው፡፡እግዚአብሔር በማንኛውም መንገድ ሥራውን ሲጀምር በአንድና በሁለት ሰዎች ሊሆን እንደሚችል ከቃሉ በብዙ ቦታ እንረዳለን፡፡ይህ ማለት ሌሎች በአጠገባቸው አልቆሙም ወይም አስተዋጽኦ አላደረጉም ማለት አይደለም፡፡

ለምሳሌ በነህምያ መጽሐፍ በራእይ ተቀባይ ነህምያና አብረው በሰሩት የየነገዱ ተወካዮች በሥራው የተሰማሩትን ቅዱሳን እንመለከታለን፡፡ በአዲስ ኪዳን ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ በተቀበለው ራእይ በኤዥያና በአውሮጳ የተተከሉት አብያተክርስቲያናት በጳውሎስና አብረውት በተሰለፉ አገልጋይ ቅዱሳኖች መተባበር እንደተሰራ እንመለከታለን፡፡ ይህችም የአማኑኤል ቤ/ክ ሥራ የቅዱሳን ጸጋና ትብብር በአንድነት የታየባት ስለሆነ በእዚህም እውነት ላይ የተተከለች ቤ/ክርስቲያን በመሆንዋ እግዚአብሔርን እናከብራለን፡፡